Government of Western Australia
Department of Health

Amharic

# የልጆች የመጫዋቻ ቦታ መሳሪያዎችን እስከ 10 ሜትር ርቀት ከሲጋራ ጪስ ነፃ ለማድረግ

ከ22 ሴፕቴምበር 2010 ጀምሮ አዲስ የወጣ የሲጋራ ማጨስ ማእቀብ

## በልጆች የመጫወቻ መሳሪያዎች አጠገብ ማጨስ የተከለከለ ነው።

በምእራብ አውስትራሊያ በልጆች መጫወቻ መሳሪያዎች 10 ሜትር ርቀት እስካለው ቦታ ድረስ ማጨስ የተከለከለ ነው።

ግለሰብ በልጆች መጫወቻ መሳሪያዎች 10 ሜትር ርቀት እስካለው ቦታ ድረስ ማጨስ አይችልም፤

- በሕዝብ ቦታዎች ወይም በከፊል የሕዝብ ቦታዎች፤ እና
- የተከለለ የሕዝብ ቦታ ካልሆነ ነው።

ይህ አዲስ ሕግ የአካባቢ የመንግሥት መናፈሻዎችን እና የአትክልት ቦታዎችን እንዲሁም የክፍለ ሃገሩ ንብርት የሆኑ መናፈሻዎችን፤ ማለትም እንደ ኪንግስ ፓርክና በየሆቴሎች የሚገኙትን የልጆች መጫወቻ መሳሪያዎችን፤ የምግብ መሸጫ ቦታዎችን እና የስፖርት ድርጅቶችን ይመለከታል።

## ምልክቶች

“ማጨስ አይቻልም” ወይም “ማጨስ ክልክል ነው” የሚል ምልክት የልጆች መጫወቻዎች ባሉበት አካባቢ ከልጆች መጫወቻዎቹ 10 ሜትር ርቀት ባለው ቦታ ላይ ማቆም ወይም መለጠፍ ይቻላል።

ማእቀቡን በተመለከተ መልክቱን ለመስተላለፍ እንዲያመች፤ የጤና ክፍል ተገቢ የሆኑ ምልክቶችን ለንግድ ቤቶችና ለአካባቢ መንግሥታት ያቀርባል።

## ተፈጻሚነት

- ከልጆች መጫወቻ መሳሪያዎች 10 ሜትር ርቀት ባለው ቦታ ማጨስ መከልከሉን ተፈጻሚ ማድረግ የአካባቢ መንግሥት ሃላፊነት ነው።
- የአካባቢ መዘጋጃ ቤቶች፤ የከባቢ የጤና መኮንኖችን ወይም ተጨማሪ መኮንኖችን፤ ለምሳሌ ሬንጀርስ በመቅጠር አዲሱ ደንብ ተፈጻሚ እንዲሆን እንዲረዳ ማድረግ ይችላሉ፤

ይህንን ጉዳይ አጽንኦት መስጠት ያስፈልጋል፤ ምክንያቱም ደንቡ ሲደነገግ የህዝብ ከፍተኛ ድጋፍ ነበረው። ካለፉት ልምዶች እንደምንረዳው፤ አብዛኛዎቹ የምእራብ አውስትራሊያ ኗሪዎች ደንቡን ተፈጻሚ እንደሚያደርጉት ይጠበቃል።

## መቀጮ

ከልጆች መጫቻ መሳሪያዎች 10 ሜትር ርቀት ባለው ቦታ ላይ የሲጋራ ማጨስ ደንብን በተላለፈ ግለሰብ ላይ የሚከተሉት መቀጮዎች ይጣሉበታል፤

| | |
|---|---|
| በፍርድ ቤት የሚጣለው ከፍተኛው መቀጮ | $1000 |
| ደንብ የመተላለፍ ማስጠንቀቂያ | $200 |

ለተጨማሪ መረጃ የትንባሆ ቁጥጥር ቅርንጫፍ ቢሮን ያነጋግሩ፤
ስልክ ቁጥር: 1300 784 892
ኢሜል: tcb@health.wa.gov.auFor more

**Disclaimer:**

The information contained in this factsheet has been produced as a guide only.

To view the full details in the relevant Tobacco Control legislation, visit www.health.wa.gov.au/tobaccocontrol

HP 11901 OCT'10